የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ፖሊሲ

መጋቢት 2008

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ .......... 4

መግቢያ .......... 4

1.1. አጠቃላይ ሁኔታ .......... 4

1.2. ጤና መሰረታዊ መብት .......... 4

1.3. የ1986 ዓ.ም.የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ እና የተገኘው ውጤት .......... 5

1.4. በፖሊሲው አተገባበር ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶች .......... 7

1.5. የጤናው ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት እና ቀጣይ የጤናው ዘርፍ ሁኔታ .......... 7

ክፍል ሁለት .......... 9

ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማ .......... 9

2.1. ራዕይ፡ .......... 9

2.2. ተልዕኮ፡ .......... 9

2.3. ግብ፡ .......... 9

2.4. ዓላማዎች .......... 9

ክፍል ሦሥት .......... 10

እሴቶች እና መርሆዎች .......... 10

3.1. እሴቶች .......... 10

3.2. መርሆዎች .......... 10

ክፍል አራት .......... 11

የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች .......... 11

4.1. የጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ማጎልበት .......... 11

4.2. ፍትሃዊ  እና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠት .......... 12

4.3. የማህበረሰብ ባለቤትነት ማረጋገጥ .......... 14

4.3. የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችንና መሰል ክስተቶችን የሚቋቋምና ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ የጤና ሥርዓትን ማጠናከር .......... 16

4.4. የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ማሻሻል .......... 17

4.5. የጤና መረጃ፣ ጥናትና ምርምር እና የእውቀት አሰተዳደርን ማጎልበት .......... 19

4.6. የመድሀኒት አቅርቦትና የህክምና ቴክኖሎጂን ማሻሻል .......... 21

4.7. የጤና ቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር .......... 23

4.8. የጤና ክብካቤ ገንዘብ ምንጭ እና አጠቃቀም ማጎልበት .......... 25

4.9. የጤና ስርዓት አመራርና አስተዳደር ማጠናከር .......... 26

4.10. የባህል ህክምና ማሻሻል .......... 28

4.11. ጤና በሁሉም ፖሊሲዎች .......... 29

4.11.1. የፖሊሲ አቅጣጫ አላማ ........ 29
4.11.2. ስልቶች ........ 30
ክፍል አምስት ........ 32
የፖሊሲው አተገባበር ........ 32
5.1. ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር ........ 32
5.2. የሕግ ማእቀፎችን ማበጀትና የማስፈጸሚያ ስልቶችን ማጎልበት ........ 33
5.3. ስትራቴጂክ እቅዶችን፣ ፖሊሲዎች፣ ፍኖተ ካርታዎችንና የአተገባበር መመሪያዎችን እንደየአስፈላጊነቱ በመንደፍ ወደ ተግባር መመንዘር ........ 33
5.4. የክትትልና ግምገማ ........ 33
5.5. የመዋዕለ-ንዋይ (የፋይናንስ) አቅርቦትና አጠቃቀም ........ 33
5.6. አስተዳደር ........ 34

# ክፍል አንድ
# መግቢያ

## 1.1. አጠቃላይ ሁኔታ

ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሀገር የሆነች በአፍሪካ ደረጃ ከናይጄርያ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሕዝብ ብዛት ያላት ስትሆን በዓለማችን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገቡ ከሚገኙት ጥቂት አገሮች አንዷ በመሆን የዜጎቿን ኑሮና የጤና ሁኔታ ለማሻሻልና ከድህነት ለማላቀቅ እየተጋች ያለች አገር ነች፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት አገሪቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ወደ አላት አገር ለማሳደግና ይህንንም ዕድገት ቀጣይ ለማድረግ አልሞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ከድህነት ወደ ብልጽግና የሚደረገው ጉዞም ብዙ ለውጥ ብቻ ሳይሆን ፈጣን ለውጥ በማስመዝገብ እምርታዊ (ትራንስፎርሜሽናል) መሆን ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ደረጃ ልማትን ለማፋጠንና የዳበረ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚቻለው የልማቱ አንቀሳቃሽ ኃይል የሆነው ሕዝብ ጤንነቱ ሲጠበቅ ነው፡፡

ስለሆነም ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊው ዕድገት ጋር የሚጣጣም፤ የህብረተሰቡን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል መሰረት ያደረገ ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ፤ ህብረተሰቡ የራሱን ጤና በራሱ በምልዓተ ህዝብ ደረጃ ለማምረት የሚያስችል የጤና ስርዓት እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት፡፡

## 1.2. ጤና መሰረታዊ መብት

ጤና ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አንዱ ሲሆን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት በተለያዩ አንቀፆች ተደንግጓል፡፡ አንቀፅ 90 ንኡስ አንቀፅ 1 "የሀገሪቱ ዓቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁሕ ውሃ፣ የመኖርያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል" ሲል የደነገገ ሲሆን በአንቀፅ 92 ንኡስ አንቀፅ 1 ደግሞ መንግሰት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንፁሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት እንዳለው በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በህገ መንግስቱ አንቀፅ 35 ንኡስ አንቀፅ 9 ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል መብት ያስቀመጠ ሲሆን እንደዚሁም በአንቀፅ 36 ንኡስ አንቀፅ 1 ስለ ህፃናት በህይወት የመኖር እና ጤንነት መጠበቅን ይደነግጋል፡፡ በአንቀፅ 44 ንኡስ አንቀፅ 1 ደግሞ ሁሉም ሰዎች ንፁሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው ይጠቅሳል፡፡

ስለሆነም በህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መሰረት እያንዳንዱ ዜጋ የጤና አገልግሎት የማግኘት መብት ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ መንግስት የጤና ፖሊሲ በመቅረፅና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ መብቶቹ እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

### 1.3. የ1986 ዓ.ም.የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ እና የተገኘው ውጤት

ኢትዮጵያ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ በአስከፊ ጦርነትና በከፋ ድህነት ውስጥ በነበረችበት ወቅት ዜጐቿ ለበርካታ የጤና ችግሮች የተዳረጉበት እንደነበር ይታወሳል፡፡ ከዚህ አንፃር አገራችን በግልና በአካባቢ ጤና ጉድለት፣ በተላላፊ በሽታዎች፣ በምግብ አለመመጣጠንና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሳቢያ የሚመጡ በርካታ በሽታዎች ምክንያት ህመምና ሞት ተንሰራፍተውባት ነበር፡፡

በደርግ ውድቀት ማግስት በተመሰረተው የሽግግር መንግስት የአገሪቱን የጤና አገልግሎት ሽፋን ከነበረበት እጅግ አነስተኛና ኢፍትሐዊ ደረጃ ለማሻሻል እና የሕዝቡን የጤንነት ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም. ተዘጋጀ፡፡ ይህ የጤና ፖሊሲ በዋና ዋና ለጤና ጠንቅ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የሕብረተሰቡን ግንዛቤ፣ እምነት፣ ባህሪና ድርጊት ለመለወጥና ብዙዎቹን የጤና ችግሮች ለማስወገድ በተለይም ደግሞ አብዛኛውን የገጠሩን ህብረተሰብ፣ አርብቶ አደሩንና ደሃ ከተሜውን ታሳቢ ያደረገና በሽታን አስቀድሞ በመከላከል ላይ ዋናው አማራጭ ያደረገ ነበር፡፡

የጤና ፖሊሲው ትግበራ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ እርከኖች በማዋቀርና ያልተማከለ አመራር እንዲኖረው በማድረግ የተጀመረ ሲሆን በ1987 ዓ.ም.የ20 ዓመት የጤናው ዘርፍ የልማት መርሐ ግብር በመቅረፅና በአራት ተከታታይ ዙሮች በማዘጋጀት መርሐግብሮቹ ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይቷል፡፡ እንዲሁም በ1997 ዓ.ም.የአገሪቱን አስፈላጊ የጤና አገልግሎት ፓኬጅ (Essential Health Service Package) በማዘጋጀት አገልግሎቱን የማስፋት ሰፊ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአገልግሎት አሰጣጡ የስራ ሂደት በተቀናጀና በተቀላጠፈ መልኩ ተጠቃሚውን ለማርካት እንዲቻል የአገልግሎት ሥርዓት መልሶ ግንባታ ጥናት /Business Process Reenginering/ በማካሄድ የጤናው ዘርፍ በሦስት ዋናዋና ክፍሎች ማለትም በአገልግሎት ሰጪ፣ አገልግሎት ተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ገዢ እይታ በማዳራጀት የሀገሪቱን የጤና አገልግሎት ለማሻሻል ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የ1986ዓ.ም. የጤና ፖሊሲ እና የጤናው ዘርፍ የልማት መርሐ ግብር የአፈጻጸም ግምገማ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ የዜጎቿን የጤና ሁኔታ ከ20 ዓመታት በፊት ከነበረበት አንጻር ከፍተኛ መሻሻል እንዳስመዘገበች በተለያዩ ጊዚያት የሚወጡ ሀገራዊና የዓለም አቀፋዊ ጥናቶችና ሪፖርቶች ይመሰክራሉ፡፡በህጻናት እና እናቶች ሞት እንዲሁም በዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች ስርጭትና የሞት ምጣኔ ላይ ከፍተኛ ውጤቶች በማስመዝገብ የምዕተ-ዓመት የልማት ግቦች ለማሳካት ችላለች፡፡

ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆናቸውን ህፃናት ሞት ከ1983 ከነበረው ስሌት ከ71% በላይ በመቀነስ የዕቅድ ጊዜው ከመጠናቀቁ 3 ዓመት ቀድሞ ለማሳካት የተቻለ ሲሆን የእናቶችን ሞት በ71% በመቀነስ ጥሩ ለውጥ ተመዝግቧል፡፡ አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በ90% የቀነሰ ሲሆን በኤች አይ ቪ ምክንያት የሚከሰት ሞት ደግሞ ከ70% በላይ ቀንሷል፡፡ በወባ ምክንያት የሚከሰተው ከ5 ዓመት በታች ህፃናት ሞት በ1983 ዓ.ም ከነበረበት በ73% ያነሰ

ሲሆን በወባ በሽታ ሳቢያ ተኝተው የታከሙ ከ5 ዓመት በታች ህጻናት ቁጥርም በ81% ቀንሷል። በቲቢ በሽታ ምክንያት የሚከሰት ሞት ምጣኔም ከ63% በላይ ቀንሷል።

የጤና አገልግሎት ስርዓቱን ለማጠናከር ሰፋፊ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን እጅግ በርካታ የጤና ተቋማት በመገንባትና የጤና ባለሞያዎች አሰልጥኖ በስራ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋን በ1987 ዓ.ም ከነበረበት 40% ወደ 100% ደርሷል።

የመጀመርያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ አሃዶች (Primary Health Care Units) እንዲጠናከሩ በማድረግ ደረጃውን የጠበቀ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ለማዳረስ ከተሰራው ሰፊ ስራ በተጨማሪ የሆስፒታል አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል ጥረት በመደረግ ለይ ይገኛል። በወረርሽኝ መልክ የሚነሱ በሽታዎች ቁጥጥር እና ፈጣን ምለሽ አሰራር በመዘርጋትና በማጠናከር በአሁኑ ጊዜ በወረርሽኝ መልክ የሚነሳ የጤና ችግር እንዳይኖር መጠነ ሰፊ የበሽታ ቅኝት ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛል።

ጤናን ለማስጠበቅም የሚውሉ ግብዓቶች ጥራታቸው፣ ብቃታቸውና መጠናቸው ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ቀርበው ተጠቃሚው አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚኖርበት ታምኖበት ይኸው በትክክል መተግበሩን የሚቆጣጠርና የሚያስተባበር መ/ቤት ከማቋቋም ባሻገር ሕብረተሰቡን የጤና አገልግሎቶችና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለቤት ለማድረግ መጠነ ሰፊ ተግባራት በመሰራት ላይ ይገኛል። የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪን ደንበኞች አገልግሎቱን በአንድ ቦታ ላይ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን የመመርመርያ መሳርያዎችና ሌሎች ግብዓቶች በማሟላት በሰባት የፊዚኮ ኬሚካል የጥራት ምርመራዎች ላይ የአለም አቀፍ እውቅናን አግኝቷል። በመሆኑም ከዚህ ላቦራቶሪ የሚወጡት የጥራት ምርመራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እምነት የሚጣልባቸው እየሆነ መጥቷል። የምግብና መድኃኒት ጥራት፤ ደህንነትና ፈዋሽነት የሚደረግ ግምገማ፣አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም፣ የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ቁጥጥር እና የሕክምና ሙከራ ቁጥጥር ስራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እያሳዩ ቢሆንም አሁንም በርካታ መሻሻሎች ሊደረግባቸው ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ በ1986 ዓ.ም የወጣውን የጤና ፖሊሲ ተክትሎ የግሉ ዘርፍ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለው አስተዋፅኦ እያደገ በመሄዱ ከፖሊሲው በፊት ጥቂት ከነበረበት በአሁን ወቅት በተለይም ደግሞ በዋና ዋና ከተሞች በሺዎች የሚቆጠሩ የግል ክሊኒኮችና በርካታ ሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም በመድሀኒት አቅርቦት ላይ በተለይም በአገር ውስጥ መድሀኒቶችን ለማምረት በሚደረገው ጥረት ውስጥ በግሉ ዘርፍ በኩል ጥሩ ጅምሮች ቢኖሩም ይበልጥ ሊጠናከር ይገባዋል።

በአጠቃላይ የተመዘገበው አመርቂ ውጤትና የጤና አገልግሎት አሠጣጥ ፍትሀዊነትና ተደራሽነትን መሻሻል ምክንያት ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ለጤናው ዘርፍ የተሰጠው የፖለቲካ አመራርና ቁርጠኝነት፣ የጤና ልማት ሰራዊት እንቅስቃሴና የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውጤታማነት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው። የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዋና ትኩረት

ግለሰብ፣ ቤተሰብና ሕብረተሰብ በራሱ የጤና ጉዳይ ራሱ ኃላፊና ባለቤት ሆኖ በሽታን በመከላከል ጤናማ ኑሮ እንዲመራና ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡፡

## 1.4. በፖሊሲው አተገባበር ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶች

የተመዘገበው ውጤት ከጤናው ዘርፍ የልማት መርሐ ግብር እና ከምእተ-ዓመቱን የልማት ግብ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ቢሆንም አሁንም ህመምና ሞት በስፋት ይታያል፡፡ የጤና አገልግሎቱ ጥራትና ፍትሃዊነት በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል ያለበት ነው፡፡ የጤናው ስርዓት ግንባታ ከፍተኛ መሻሻል የታየበት ቢሆንም አሁንም በርካታ ተግዳሮቶች አሉ፡፡ የሰው ሃይል ፍላጎትን ለማሟላት የተደረገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም የሰው ሃይል ስብጥር እና የሞያ ብቃት ላይ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡

የጤናው ዘርፍ መዋዕለ-ንዋይ ፍላጎት 34 % የሚሸፈነው ከውጭ በተገኘ ዕርዳታ ሲሆን ይህም በቀጣይ አስተማማኝና ዘላቂ የጤና አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ስጋት እነደሆነ ቀጥሏል፡፡ እንዲሁም የጤናው ዘርፍ የሚያስፈልጉትን የመድሀኒት፣ ህክምና መገልገያ መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ያለማቋረጥ የማቅረብና የጥራት ደረጃቸውን አስተማማኝ የማድረግ መጠነ-ሰፊ ስራ መሰራት እንዳለበት ይታመናል፡፡

## 1.5. የጤናው ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት እና ቀጣይ የጤናው ዘርፍ ሁኔታ

ከ20 ዓመታት በላይ በስራ ላይ የሚገኘው የጤና ፖሊሲ እንዲከለስ የተደረገበት ምክንያት ከ1986 ዓ.ም ወዲህ በርካታ አገራዊ፣ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ሁናቴዎች በመለዋወጣቸው እነዚህን ለውጦችና ተሞክሮዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት በማስፈለጉ ነው፡፡ በተጨማሪም አብዛኞቹ የጤና ችግሮች መፍትሄ ያላቸው ቢሆኑም መፍትሄዎቹን ለችግሩ ተጠቂዎች ለማድረስ አሁን ያለው የጤና ስርዓታችንን እምርታዊ በሆነ መልኩ ማሻሻል በማስፈለጉም ነው፡፡

አዲሱ የጤና ፖሊሲ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት፣ የስነ ህዝብ ሁኔታዎችን፣ የከተማዎችና የኢንዱስትሪ መስፋፋትን፣ ግሎባላይዜሽን፣ የአየር ጠባይ ለውጥና የቴክኖሎጂ ለውጦችን፣ ከምግብ እጥረትና ከመጠን በላይ ውፍረትን በህብረተሰብ ጤና ላይ ያለውን ተጽእኖ፣ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭት እና በተለያዩ ምክንያት የሚያጋጥሙ አደጋዎች በጤና አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ጣምራ ጫና ሊሆኑ እንደሚችሉ ከግንዛቤ በማስገባት እነዚህን ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የፖሊሲ ማዕቀፍ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

አዲሱ ፖሊሲ የህዝቦችን ብልጽግናና የአገሪቱን እድገት እውን የሚያደርግ ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ በማድረግ የበለጸገች አገር ለመፍጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ የጤናው ዘርፍ የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት እና የኢኮኖሚ እድገቱ ውጤት የዜጎችን ጤናና ደህንነት ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረሱን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

የአገራችን ራዕይ በሕዝቦች ተሳትፎና መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የጤናው ፖሊሲ የአገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ በማጎልበት ሀገሪቱ የፈጣን ልማትና እድገት ተጠቃሚ እንድትሆን የጐላ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የጤና ፖሊሲው የህገመንግስት ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገው የዜጎች መብት ይበልጥ በማጠናከር አሁን ያለው የአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት አካል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

# ክፍል ሁለት
# ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዓላማ

## 2.1. ራዕይ፡

*ጤናማ፣ ምርታማና የበለጸገ ኅብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ነው፡፡*

## 2.2. ተልዕኮ፡

*ጥራቱን የጠበቀ፤ ፍትሐዊና ተደራሽ የሆነ የጤና ማበልጸግ፣ በሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምና፣ የተሃድሶና ክብካቤ የጤና አገልግሎት በመስጠትና በመቆጣጠር የኢትዮጵያውያንን ጤናና ደህንነት ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነው፡፡*

## 2.3. ግብ፡

*ሁሉአቀፍ የጤና አገልገሎት ተደራሽ በማድረግ እና ዜጎች በጤና ችግር ምክንያት ለኢኮኖሚ ቀውስ በማይዳርግ መልኩ አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ እንዲሁም ጤናን በሁሉም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አጠቃላይ የልማት ፖሊሲዎች በማካተት የኢትዮጵያውያንን ጤናና ደህንነት የላቀ ደረጃ ላይ ማድረስ፡፡*

## 2.4. ዓላማዎች

*የጤና ፖሊሲው አጠቃላይ አላማ ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት በጤና ውጤታቸው ከላቁት ጋር ተመጣጣኝ የጤና ሁኔታ እንዲኖራት ማስቻል ሲሆን ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡*

- ✓ *ጥራት ያለው ሁሉአቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ለማረጋገጥ*
- ✓ *መከላከል በሚቻሉ ምክንያቶች የሚደርሱ የእናቶችና ህጻናት ሞት ለመግታት፤*
- ✓ *ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ማዕከል በማድረግ ተላላፊ፣ ተላላፊ ያልሆኑና በተለያዩ አደጋዎች ሳቢያ የሚደርሱ ህመምና ሞትን ለመቀነስ፤*
- ✓ *አማካኝ የመኖር እድሜ ጣርያን ለማሳደግ*

# ክፍል ሦሥት
# እሴቶች እና መርሆዎች

## 3.1. እሴቶች

1. የማህበረሰብ ጥቅሞችን ማስቀደም
2. ቅንነት፣ ታማኝነትና ሐቀኝነት
3. ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና ምስጢር መጠበቅ
4. አድልዎ አለመፈፀም
5. ሕግን አክባሪነት
6. አርአያነት
7. መደጋገፍ
8. ለሙያዊ ሥነ-ምግባር ተገዢ መሆን
9. ለለውጥ ዝግጁነት
10. ርህራሄ

## 3.2. መርሆዎች

- ትኩረት ለጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል
- ሁሉአቀፍ ተደራሽነት
- የማህበረሰብ ባለቤትነት
- ትኩረት ለመሠረታዊ ጤና አገልግሎት
- ራስን መቻል
- ህሙማንን/ታካሚ/ተጠቃሚ ማዕከል ያደረገ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት
- ፍትሀዊነት
- መልካም አስተዳዳር
- የፆታ እኩልነት
- እናቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ተኮር
- አሳታፊ አጋርነት
- ዘወትር የሚማርና ለውጥን የሚቀበል የጤና አገልግሎት ስርዓት
- ሙያዊ ግዴታና ሥነ-ምግባር
- ዘርፈ ብዙ ትብብር

# ክፍል አራት
# የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች

## 4.1. የጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ማጎልበት

ባለፉት ሃያ ዓመታት ጤናን በማበልፀግ፣ በሽታን በመከላከል እና መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት ተደራሽነት በማሻሻል ላይ ባተኮረ የጤና ፖሊሲና ስትራቴጂዎች መሰረት በማድረግ መጠነ ሰፊ የመስረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማት በመገንባትና የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል በማፍራት የጤና አገልግሎት ተደራሽነቱን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ ይህም የዜጎች የጤና ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻል ምክንያት ሆኗል፡፡

በቀጣይም ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል የጤና ፖሊሲው ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን በተለይም እየጨመረ የመጣውን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች፣ አሁንም ከፍተኛ በሚባል ደረጃ ያሉትን ተላላፊ በሽታዎች እንዲሁም ትኩረት የሚሹ የሀሩርና ሞቃታማ በሽታዎችን ስረጭትን ለመግታት ብሎም ከህብረተሰብ የጤና ችግርነት ለመፋቅ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል፡፡

የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱ ቀጣይነት ባለው የተቀናጀ የጤና ማበልፀግና በሽታን መከላከል ለማጠናከር እንዲቻል የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የማስፋትና የማጠናከር ስራ ይሰራል፡፡ በአጠቃላይ የጤና ማበልፀግና በሽታን መከላከል በሁሉም የጤና አገልግሎት እርከኖች ማለትም በሁሉም የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት አሃዶችና በሆስፒታሎች እንዲኖርና እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡ በቀጣይ የሚዘጋጁ ስትራጂዎችም የፖሊሲውን ጭብጥ መሰረት ያደረጉ፣ ሁሉን አቀፍ እና የህብረተሰቡን የጤና እና ጤና ነክ ፍላጎቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ፤ እንዲሁም የህብረተሰቡን ፍላጎት ምላሽ የሰጡ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### 4.1.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

በህብረተሰቡ ባለቤትነት የጤና ማበልፀግንና በሽታ መከላከልን በማስፋትና በማጠናከር ህብረተሰቡ የራሱን ጤና በራሱ በምልዓተ ህዝብ ደረጃ እንዲያመርት ማድረግ ነው፡፡

### 4.1.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማሕበረሰብ ደረጃ የሚተገበሩ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎች እና ጤናማ ባህሪያትን የሚያበረታቱ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርሃግብሮችን ማጠናከር፤
2. ለበሽታዎች የሚያጋልጡ ክስተቶች በመቆጣጠርና ተጋላጭነትን በመቀነስ የበሽታዎች ክስተት መከላከልና ስርጭት መግታት፤ እንዲሁም በሽታው ሲከሰት አላስፈላጊ ስቃይና ጉዳት እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የጤና አገልግሎትን ማጠናከር፤

3. የባህሪ ለዉጥ የሚያመጣ ተግባቦት ክህሎቶችን እና ሌሎች የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ማሕበረሰቡ የራሱን የጤና ችግሮች ከነመፍትሔዎቻቸዉ ለይቶ እንዲያዉቅ በማስቻል እና የተለያዩ የሐይጅንና ሳንቴሽን ማስፋፊያ አማራጮችን በመጠቀም የገጠሩን ማሕበረሰብ ሐይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ማሻሻል፤
4. ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በጥናት እና መረጃ ላይ የተመሰረተ የሐይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ስራዎችን በማጠናከር የከተማ ሐይጅን እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ማሻሻል፤
5. ሁሉአቀፍ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎትን ተደራሽነትና የጥራት ደረጃ የሚያሻሽሉ ስትራቴጂዎችና የማስፈጸሚያ ስልቶችን በመንደፍ በስፋት መተግበር፤
6. የጤና አገልግሎት አሰጣጡ በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት (Primary Health Care) መርህ የተመሰረተ ሁሉን አቀፍ፣ ፍትሃዊ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ እና የህብረተሰቡን ባለቤትነት ያረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ፤
7. የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት አሀዶች በማጠናከር የመጀመርያ የጤና ክብካቤ ማጠናከርና በቀጣይም ቤተሰብ መሰረት ያደረገ አገልግሎት ደረጃ እንዲደራጅ ደረጃ በደረጃ መስራት፤
8. የጤና አገልግሎት አሰጣጡ የእናቶችና ህፃናት ጤና ማሻሻል፤ ስርዓተ ምግብን ማሻሻል፤ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር፤ የአእምሮ ጤና ማሻሻል፤ የተለያዩ አደጋዎች መከላከለና መቆጣጠር ላይ ትኩረት ማድረግ ናቸው፡፡

## 4.2. ፍትሃዊ እና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠት

ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የጤና አገልግሎት አደረጃጀት እንደየአስፈላጊነቱ የሚያስፈልጋቸውን ተቋማት፣ የሰው ኃይል እና ሌሎች ግብአቶች በሟሟላት ተደራሽነቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር የተደረገ ሲሆን የተለያዩ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ሪፎርሞችን በመቅረፅና በመተግበር ከፍተኛ መሻሻሎች እንዲመጡ ተደርጓል፡፡

በቀጣይም የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያረካ የሚችል የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሀዊ ተደራሽነትን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚሰሩ ስራዎች ከፍተኛ አጽንኦት ይሰጣቸዋል፡፡ለዚህም የሚውል የግብዓት እና የሰው ኃይል የሃገሪቷ አቅም በፈቀደ መጠን በተቀናጀ መልኩ እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

የጤና አገልግሎት አሰጣጡ ሁሉአቀፍ፣ ፍትሃዊ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ እና የህብረተሰቡን ባለቤትነት ያረጋገጠ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የህዝቡን ጤንነት ከመጠበቅ እና የአገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የተመረጡ የጤና አገልግሎቶች መንግስት በነፃ የሚሰጥበት ወይም የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ሁኔታዎች በፈቀዱ ያህል ድጎማ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም በህብረተሰብ ጤና አደጋዎችና ቁጥጥር ዙሪያ እና ከሌሎች ሴክተሮች ጋር የሚሰሩ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ በትኩረት ይሰራል፡፡ የጤና አገልግሎት ሥርዓቱ ማንኛውንም የአደጋ ክስተቶችን አስቀድሞ በመተንበይና በመከላከል አደጋዎች ቢከሰቱም በፍጥነት መንስኤዎችን በመለየት ፈጣን እና ውጤታማ ምላሽ በመስጠት የመሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች ሳይቋረጡ የማህበረሰቡ ኑሮ እና ማህበራዊ ዕሴቶች ሳይዛቡ እንዲቀጥሉ በማድረግ የተጐዱ ወገኖችም ተገቢውን እንክብካቤና መልሶ መቋቋም የሚችል፣ በአጠቀላይ አደጋዎችንና መሠል ክስተቶችን መቋቃም የሚችል የጤና አገልግሎት ሥርዓት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ በመሰረታዊ ጤና አገልግሎት (Primary Health Care) አማካኝነት የጤና አገልግሎቶችን ሁሉ-አቀፍ ተደራሽነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የጤና አገልግሎት አደረጃጀቱ የተቀናጀ የጤና ማበልፀግ፣ በሽታን መከላከል፣ የፈውስ ህክምናና የተሃድሶ አገልግሎት ተመጋጋቢ በሆነና ቤተሰብንና ማህበረሰብን ማእከል ባደረገ መልኩ በተሳለጠ መንገድ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

### 4.2.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ የተቀናጀ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ በሁሉም የጤና አገልግሎት ደረጃዎች እንዲኖር በማድረግ የጤና እንክብካቤውን ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል እንዲጠቀምበት ማረጋገጥ ነው፡፡

### 4.2.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. ጥራቱን የጠበቀ የተቀናጀ የጤና አገልግሎት ፍትሃዊ ተደራሽነትን የሚያረጋግጥ የአገልግሎት ሥርዓት ማጠናከር፤
2. የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት አሀዶች ከሆስፒታሎች ጋር በተጣጣመና የተገልጋዩን ፍላጎት በሚያረካ መልኩ የሚሰሩበት የተሳለጠ አሰራር እንዲኖር ማድረግ፤
3. የድንገተኛ ህክምና ስርዓት በተሟላ መልኩ በመዘርጋት ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን አገልግሎት ማመቻቸት፤
4. የግሉ ዘርፍ በጤና አገልግሎቱ በተለይም በስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አገልግሎት ላይ እንዲሰማሩ ማበረታታት፤
5. የጤና ተቋማት አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል የተጀመሩ ሪፎርሞችን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገርና አገልግሎት ጥራትን ይበልጥ የሚያሳድጉ አሰራሮችን መዘርጋት፤
6. ዓለም አቀፍ የምዘና ደረጃዎችን በማሟላት የህክምና አግልግሎት ጥራት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ተቋማትን የማፍራት ስራን በትኩረት መተግበር፤
7. ጥራት ያላቸው አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፤

8. የጤና አገልግሎትን ለሁሉም ዜጋ በጾታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ እና ሌሎች ልዩነቶች ሳቢያ አድልዎና መገለል ሳያደርጉ በእኩልነት ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
9. የጤና አገልግሎቱ የአካል ጉዳትና ልዩ ፍላጎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን በተገቢ ሁኔታ ለማገልገል የሚያስችል እንዲሆን ማድረግ፤
10. ለሚከተሉት የሕብረተሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎት ፍላጎት ልዩና ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል፡
    - ለቤተሰብ በተለይ ለሴቶች፣ህጻናት፣ ወጣቶችና ለአረጋውያን
    - በግንባር ቀደምትነት በማምረት ተግባር ላይ ለሚሳተፉ
    - ለአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ፣ለአርብቶ አደሩ፣ ለድሃ ከተሜዎች፣
    - በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተጠቁ

## 4.3. የማህበረሰብ ባለቤትነት ማረጋገጥ

ጤናው የተጠበቀ ህዝብ ለአንድ አገር ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት እሙን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሰው ኃይል በከፍተኛ ግብዓትነት የሚጠቀም በመሆኑ የአምራች ዜጋውን ጤና የተሻለ ማድረግ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለሆነም የአገራችንን ፈጣን የልማት ጉዞ ለማስቀጠል እንዲቻል በማህበረሰቡ ከፍተኛ ንቅናቄ አማካኝነት በጤና ችግሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ጤናማ ዜጋን የመፍጠር ራዕያችንን መሳካት ግድ ይላል፡፡

ኢትዮጵያ ማህበረሰቡ የራሱን ጤና በራሱ እንዲያስጠብቅ የጤና ስራዎችን በባላቤትነት እንዲመራ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችንና የአተገባባር ስልቶችን በመንደፍ በስፋት በማስረጽ ትታወቃለች፡፡ የእያንዳንዱ ቤተሰብና ግለሰብ ጤና በማህበረሰቡና በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት፣ እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህልን የማጎልበትና በራሱ የጤና ጉዳዮች ላይ ራሱ መወሰን እንዲችል የማመቻቸት ሁኔታን በመፍጠር ረገድ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ምሰሶ የሆነው የጤና ኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በባለቤትነት የተሳተፈባቸው ስራዎች ውጤታማነታቸው የላቀ መሆኑን ባለፉት አስር አመታት የተመዘገቡትን የጤና ውጤቶች ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ የምዕተ-ዓመቱን ግቦችን ለማሳካት ከቻለችባቸው ምክንያቶች መካካል ዋነኛው የማህበረሰቡ በባለቤትነት የጤና ስራዎች በመተግበሩ ነው፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር የእያንዳንዱ ቤተሰብ በባለቤትነት መሳተፍን ማዕከል ያደረገ በመሆኑ በጤናው ዘርፍ የልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባር አድርጎ በመውሰድ ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ሆኖም በከተሞችና በአርብቶ አደር አከባቢ የጤና ኤክስቴንሽን መርሀ-ግብር አፈፃፀም እንደተጠበቀው ባለመሆኑ የማህበረሰቡን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ብዙ ስራ መስራት የሚጠይቅ ነው፡፡

በመሆኑም ቀጣይ ስትራቴጂዎችና የአተገባባር ስልቶችም ይህንን የማህበረሰቡ ባለቤትነት ግብ የበለጠ የሚያጠናክሩና ከማህበረሰቡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ይህንንም ተጨባጭ ለማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶች በመጠቀም በተለይም ሴቶችን ማዕከል ያደረገው የልማት ሰራዊት እንቅስቃሴ ይበልጥ በማጠናከርና የማህበረሰቡን ባለቤትነት በማሻሻል በሁሉም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ትኩርት አድርጎ እንዲንቀሳቀስ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡ በየልማት ሰራዊቱ እና አደረጃጀቶች በመጠቀም በጤና ተቋማት በጎ ተፅእኖ እንዲያሳርፍ በማድረግ የጤና አገልግሎቱ ጥራትና ፍትሃዊ ተደራሽነት እንዲሻሻል በማድረግ ሂደት ቁልፍ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል።

### 4.3.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

የራሱን ጤና የሚያመርት ማህበረሰብ መፍጠር ነው።

### 4.3.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. ራስን የመቻል ዓቅም በመገንባት የማህበረሰቡ ባለቤትነት ማጠናከር፤
2. የህብረተሰቡን ብዝሀነት፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ሌሎች ልዩነቶችና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረጉ የጤና መርሀ ግብሮችን እንደየአካባቢውና ህበረተሰቡ ፍላጎት በህብረተሰቡ ባለቤትነት መቅረጽና መተግበር፤
3. የልማት ሰራዊቱን አደረጃጀት በመጠቀም እና ለለውጥ ዝግጁ እንዲሆን በማስቻል ሁሉንም የጤና ፓኬጆች ትግበራ በማጎልበት በንፁህ፣ ፅዱ እና ምቹ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ሞዴል ቤተሰቦች፣ ቀበሌዎች ብሎም ወረዳዎች ማፍራት፣ ማስፋት፤
4. የተለያዩ ህጋዊና ባህላዊ የማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶችን በማጠናከር በዘርፉ ዕቅድ ዝግጅት፣ በትግበራ እንዲሁም በግምገማ ውስጥ በተጠናከረ መልኩ በማሳተፍ የማህበረሰቡ የውሳኔ ሰጪነት ሚና ማጎልበት፤
5. በማህበረሰብ ደረጃ ዘርፈ-ብዙ አጋርነትን በማጠናከር የማህበረሰቡን የጤናና ጤና ነክ ጉዳዮች ባለቤትነት ማጠናከር፤
6. የማህበረሰቡን ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ሁኔታዎችን የሚታደግና በጤናው ዘርፍ ስራዎች ላይ የባለቤትነት ሚናቸውን የሚያጎሉ የህግና የአሰራር ከለላዎችን ማድረግ፤
7. የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መረጃን በመጠቀም ማህበረሰቡን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፍ እንዲሁም መረጃን በመጠቀም የራሱን ጤንነት የማምረት ሂደት እንዲመራ፣ እንዲተገብር ማስቻል፣
8. የሴቶችን በራሳቸውና በቤተሰባቸው ጤና ዙርያ የውሳኔ ሰጪነት ሚና ማጎልበት።
9. ከባህላዊ ልማዶችና ድርጊቶች ጎጂዎቹን በመለየትና በማስቀረት ጠቃሚ የሆኑትን ማጎልበት፤

## 4.3. የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችንና መሰል ክስተቶችን የሚቋቋምና ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ የጤና ሥርዓትን ማጠናከር

የጤና አገልግሎት ተገቢውን የጥራት እና ደረጃ በጠበቀ መልኩ ተደራሽ እንዲሆን በዘላቂነት ሊቀጥል የሚችለው በማንኛውም ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ ወረርሽኞችን፣ ከድርቅ ጋር የተያያዙ የምግብ እጥረት የጤና ችግሮች፣ ድንገተኛ የአደጋ ክስተቶችን አስቀድሞ መተንበይ መከላከልና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚችል ሥርዓት መዘርጋት ሲቻል ነው። ይህ የአደጋ መከላከልና ቁጥጥር ሥርዓት አየተጠናከር ከመጣው ብሔራዊና አለምአቀፋዊ የጤና ደህንነት ሥጋት አንፃር ቁልፍ ሚና የሚጫወት ሥርዓት ይሆናል።

ባለፉት ሁለት አስርት አመታት በአለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ የመጣውን ሁለንተናዊ የአደጋ ክስተቶችን እና ሥጋቶችን ባገናዘበ መልኩ በጤናው ዘርፍ በተደረገው ማሻሻያ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ማዕከል ተቋቁሞ በወረርሽኝ መለየትና መከላከል እንዲሁም ፈጣን ምላሽ በመስጠት ረገድ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል። ይሁን እንጂ የህብረተሰቡን ጤና ለአደጋ የሚያጋልጡ ክስተቶች በወረርሽኝ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆን የአደጋ መንሴኤዎች በሁሉም ሴክተሮች የሚታዩ እና ሊከሰቱ የሚችሉ እና ሁለገብ ምክንያቶች በመሆናቸው የሁሉንም ሴክተሮች አሣታፊ የሆነ እና ጠንካራ ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ ነው።

ይህ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ሥርዓት በዋነኛነት የሚያከናውናቸው ተግባራት፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቅኝት ማካሄድ፣ ሥጋቶችን አስቀድሞ መለየት፣ ክትትል ማድረግና የአደጋ ቅድመ ማስጠንቀቂያዎችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን መለየት፣ የመከላከል ሥርዓቱን ማጠናከር፣ የአደጋ ቁጥጥር ዝግጁነትን ማጠናከር ፈጣንና ውጤታማ የሆነ ምላሽ መስጠት እንዲሁም የአደጋ ጉዳተኞችን መልሶ ማቋቋምና መሠረታዊ የጤና እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ሣይቋረጡ መቀጠላቸውን ማረጋገጥ ይሆናል፣ ከዚህ በተጨማሪም ለፖሊሲ እና ስልታዊ አቅጣጫዎች መረጃ እና ትንታኔ ማቅረብንም ያጠቃልላል።

ይህም ሥርዓት አደጋን ከመተንበይ እና ምላሽ ከመስጠት ባሻገር ተገላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት፡ የህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶችን፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፣ ፀጥታ እና ደህንነትን በማስጠበቅ እና በመጠበቅ ረገድ ቁልፍ ሚናን ይጫወታል።

### 4.3.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

በህብረተሰብ ባለቤትነት የሚመራ ህብረተሰብንና አገርን ከወረርሽኝ እና ሌሎች የድንገተኛ አደጋ ክስተቶችን የሚከላከል እንዲሁም አደጋዎች ሲከሰቱ ፈጣን ምላሽ የሚሠጥ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር።

### 4.3.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሣካት መንግስት የሚከተሉትን ሥልቶች ይተገብራል፣

1. ፈጣን እና ጊዜውን የጠበቀ ድንገተኛ አደጋዎች የቅኝት እና የኩነት ክትትል ሥርዓት እና ወቅታዊ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መዘርጋት፤
2. አስቀድሞ በመከላከል፣ ፈጣን ምላሽ በመስጠት እና የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ጉዳት እና ተፅእኖ ለመቀነስ የሚያስችል ሁለገብ የሆነ የአደጋ ክስተት ሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓትን ማጠናከር፤
3. ወቅታዊ የሆነ የሥጋት እና የተጋላጭነት መረጃ መያዝ እና ለድንገተኛ አደጋ የሚሆኑ ፈጣን የግብአት አቀርቦት ሥርዓትን መፍጠር፤
4. በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች ሳይቋረጡ የሚቀጥሉበትን ሥርዓት መፍጠር፤
5. የድንገተኛ አደጋዎች መከላከል፣ መለየትና ፈጣን ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ በየደረጃው አቅም መገንባት እና በአካባቢው በሚገኝ  አቅም ፈጣን ምላሽ እንዲሠጥ ማስቻል፤
6. ህብረተሰቡን በማሳተፍ በተለይም በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ምላሽ ወቅት የህብረተሰቡን የባለቤትነትና ኃላፊነት መፍጠር፤
7. ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የእንስሳት ጤና ላይ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጤና አደጋዎች ዝግጁነት እና ምላሽ አሰጣጥ ላይ በጋራ መስራት፤
8. ህብረተሰብን ከወረርሽኝ እና ሌሎች የድንገተኛ ክስተቶች መከላከልና መቋቋም የሚችል እንዲሁም ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ እና የመሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች ሳይቋረጡ እንዲቀጥሉ የሚያስችል  የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር፤
9. በተፈጥሮም ሆነ በሰዉ ሰራሽ አዳጋዎች ወቅት እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ የሴክተር መስሪያ ቤቶች እና አጋር አካላት ጋር በመተባበር ፈጣን ምላሽ መስጠት፤
10. በየደረጃው ያለውን የመረጃ ልውውጥ፣ የቁጥጥር እና ግምገማ ሥርዓት ማጠናከር፤
11. አለምአቀፍ የመረጃ ልውውጥ ማጠናከር፤እንዲሁም ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ያለውን ትብብር በማጠናከር የህብረተሰቡን የጤና አደጋዎች ጉዳትና ተፅእኖ መከላከል፤
12. የሕብረተሰብ ድንገተኛ የጤና አደጋዎች የላባራቶሪ የመመርመር ዓቅም ማጎልበት፤
13. ለሕብረተሰቡ አደገኛ የሆኑ ወይም ሊሆኑ የሚችሉ እንስሳትና ንጥረነገር ለይቶ በማቆየት የዜጎችን ጤንነት መጠበቅ፤

## 4.4. የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ማሻሻል

ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት ለጤናው ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት በተሰጠው ትኩረት በርካታ የጤና ባለሙያዎች ሰልጥነው ወደ ስራ ተሰማርተዋል፡፡ እስከአሁን በተደረገ ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን፣ ነርሶችን፣ ላቦራቶሪና

ፋርማሲ ባለሙያዎችን በማፍራት አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ እጥረት ባላባቸው የጤና ሙያዎች ባለሙያዎችን የማሰልጠኑ ስራ በተፋጠነ መልኩ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የሐኪሞች፣ ሰመመን ሰጪ ባለሙዎች፣ እና አዋላጅ ነርሶች እንዲሁም ሌሎች ጤና ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ወደ ስራ የማሰማራት ተግባራት እየተከናወኑ ሲሆን የስፔሻላይዜሽን ስልጠናዎችን በየደረጃው በስፋት ለመስራት ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የ20 ዓመት የጤናው ዘርፍ ሰው ኃይል ልማት እቅድ በማዘጋጀት የዘርፉን የሰው ሀብት ፍላጎት ለማርካት በርካታ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች የተከፈቱ ሲሆን የተማሪ ቅበላ አቅማቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ ይገኛሉ፡፡ ይህ በእዚህ እንዳለ አሁንም የሰው ኃይል ብዛት፣ ስብጥር፣ ፍትሀዊ ድልድልና ጥራት ዙሪያ የሚፈለገውን ያህል ለመድረስ በቀጣይ የጤናው ዘርፍ ሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂክ እቅድን በመከለስ የዘርፉን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የሰው ሃብት ልማት ፍኖተ-ካርታ፤ የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂዎችና ማስፈጸሚ ስልቶች በማዘጋጀት የላቀ ክህሎት፣ በሙያ ስነምግባራቸው ምስጉን የሆኑና ወገናቸውን ለማገልገል ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ያላቸው ባለሙያዎችን ለማፍራት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋራ መጠነ ሰፊ ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም የባለሙያ ፍልሰትን ለመቀነስና ፍትሀዊ ስርጭትን ለማሻሻል የሚረዱ የአሰራር ስርዓት እንዲበጅ ይደረጋል፡፡

ቀጣይ የሰው ኃይል እቅድ ዝግጅትን በመረጃ የተደገፈ፣ የማሰልጠኛ ተቋማትን ብቃት በማሳደግ ጥራት ያላቸው ባላሙያዎች በተመጣጣኝ ቁጥርና ጥራት እንዲያፈሩ፣ የሰው ኃይል አስተዳደሩም ፍትሀዊ የሰው ኃይል ምልመላ፣ ምደባና፣ ማትጊያና ተከታታይ ስልጠና እንዲኖር በማድረግ እንዲሁም የሰው ኃይል ምዝገባና ቁጥጥርን በማጠናከር ዙሪያ የጎላ ሚና እንዲኖራቸው ተደርጎ መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.4.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

ህብረተሰቡን በተገቢው ሁኔታ ለማገልገል የሚችል ብዛትና የሙያዊ ስብጥሩ የተሟላ፤ በአመለካከትና በሙያ ስነምግባር የታነፀ እና ብቃት ያለው ባለሙያ እንዲኖር ማስቻል፡፡

### 4.4.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. አገራዊ የሰው ሃይል ፍላጎትንና ዓለም አቀፋዊ የሰው ኃይል የገበያ ሁኔታን ከግምት በማስገባት የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂን በመቅረጽ የሚፈለገውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ጥራትና ስብጥር ለማፍራት በትኩረት መስራት፤
2. የሰው ኃይል ልማት ስርዓቱ ወደ ጤና ዘርፍ የሚገቡ ባለሙያዎችን የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድሙና የአገልጋይነት መንፈሳቸው የላቀ እንዲሆንና ለሙያው ተገዥነታቸው የዳበረ እንዲሆን በመጀመሪያና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ ግንዛቤያቸውን በማስፋት ወደ ጤና ማስልጠኛ ወይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሲገቡ ከውጤታቸው በተጨማሪ ለሙያው ያላቸውን ፍላጎት በመዳሰስ የሚያስችል

የተማሪዎች ምልመላና በሥራ ዓለም ላይም ይህንኑ የአገልጋይነት ማስረጽ የሚችል ስርዓት መዘርጋት፤

3. በጤናው ዘርፍ የተሰማራው የሰው ሃይል ህብረተሰቡን በተገቢው ሁኔታ ለማገልገል እንዲችል በአመለካከትና በሙያ ስነምግባር ማነፅ፤
4. በጤና እንክብካቤ የቡድን አሰራርን የሚያዳብር ሥርዓት ማጠናከር፤
5. የሰው ኃይል ልማት አስተዳደር የጾታ፣ የባህልና ሌሎች የማህበረሰብ ልዩነትን ታሳቢ በማድረግ ፍትሀዊ የጤና አገልግሎት እንዲኖር ማስቻል፤
6. የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ታሳቢ ያደረገ የሰው ሃይል ልማትና አስተዳደር ላይ ትኩረት በመስጠት ብቃት ያላቸው የጤና ባለሙያዎችና አመራሮች በማፍራት ህብረተሰቡን ማገልገል፤
7. በጤናው ዘርፍ ሴት ባለሙያዎችን በብዛት በማፍራት የሰው ኃይል የጾታ ስብጥሩን ወደ ሴቶች ያጋደለ ማድረግ፤
8. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አቅም በማጠናከር የጤና ባለሙያዎችን የጥራት ደረጃና ብቃት የላቀ ደረጃ ላይ ማድረስ፤
9. ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና በተጠናከረ መልኩ በመተግበር ባለሙያዎች የሙያ ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ እና ከምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ ጋር እንዲሁም ከጤና ባለሞያዎች የዕድገት መሰላል ጋር ማስተሳሰር፤
10. በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጤናው ዘርፍ በአገራቸው እየተካሄደ ያለው የጤና ስርዓት ግንባታና የጤና አገልግሎት አጋዥ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
11. የሰው ኃይል ልማት አስተቃቀድ፣ አተገባባር፣ ክትትልና ቁጥጥር ለማሻሻል የአቅም ግንባታ ስራዎችን በየደረጃው ማጠናከር፤
12. የሰው ሀብት መረጃ አያያዝ በተመለከተ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ በማድረግ ዘርፉ የተሟላ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ እና ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውል ማስቻል፤
13. በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሰሩ የጤና ባለሞያዎች እንደአገልግሎቱ ሁኔታና ተፈላጊነት ልዩ የማትግያና ማበረታቻ መንገዶች በመዘርጋት ተጠቃሚ ማድረግ፤
14. በሙያ ብቃታቸውና ሥነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መሰረት የተለያዩ የማትግያና ማበረታቻ መንገዶች በመዘርጋት ተጠቃሚ ማድረግ፤

## 4.5. የጤና መረጃ፣ ጥናትና ምርምር እና የእውቀት አስተዳደርን ማጎልበት

የጤናውን ዘርፍ በእውቀትና በመረጃ ለማስተዳደርና ለመምራት የጤና አስተዳዳር መረጃ ስርዓት፣ ምርምርና ልማት የሚኖራቸው ፋይዳ የጎላ እንደሆነ ይታወቃል። የጤናና ጤና ነክ ውሳኔዎችን በመረጃ የተደገፉ ለማድርግ በተሰሩ ስራዎች የተጠናከረ አጋርነትንና የተቀናጀ አሰራርን ለማሻሻል፣ የጤና ስርዓቱ ዋና ዋና ማነቆዎችን ለመለየት፣ የስራ አፈጻጸምን ለመከታተልና ለመገምገም፣ የጤና መረጃ ለመሰብሰብ፣ የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል፣

የበሽታና ሌሎች ጤና-ነክ ቅኝቶች ለማገዝ፣ የስተራቴጂና አመታዊ እቅዶችን ለማዘገጀት፣ ሀብት ለማሰባሰብ ለማደላደልና አጠቃቀማቸውን ለመከታተል አስችሏል፡፡ ሆኖም በዘርፉ የሚገኙትን ተቋማት በማያባራ የመማርና ዘወትር ለመሻሻል የሚተጉ ለማድረግ መረጃን የመሰብሰብ፣ የመተንተንና ወደ እውቀትና ክህሎት በመመንዘር ጥቅም ላይ በሚውል መልኩ የማቅረብና ለቀጣይ ስራዎች መደላድል እንዲሆኑ በወጉ አደራጅቶ የማስቀመጥ ስራዎች (Knowledge Mangement) የሚፈለገውን ያህል ባለመሆኑ በትኩረትና በስፋት መሰራት ይኖርባቸውል፡፡

የጤና ምርምሮች የሚያደርጉ ኢንስቲቱዩቶችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ በርካታ ባለድርሻ አካላት አሉ፡፡ በእነዚህ ተቋማት የጥናትና ምርምር ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም ውጤቶችን ወደተግባር የመተረጎም አቅም ላይ ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡ በጥናትና ምርምር ህትመቶች ረገድም አገራችን ከሌሎች አገራት ጋር ስትነጻጸር ዝቅተና በሚባል ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ የጤናና ጤና ነክ ጥናትና ምርምር አጀንዳዎችን አጣጥሞና አቀናጅቶ ለመከወን የሚያስችል የአቅም ግንባታና ማስተባበር ስራዎች ዙሪያ ትኩረት በመስጠት ሀገራዊ የሆኑ መሠረታዊ መረጃዎችንና የምርምር ውጤቶችን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ የዕድገት ግስጋሴያችንን አሰተማማኝ ደረጃ ያደርገዋል፡፡

### 4.5.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት ወደተሻለ ደረጃ የሚያደርሱ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ፣ የጤና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመዳሰስና ከአገራችን ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ወደተግባር በመተርጎም እንዲሁም የጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን አያያዝና አጠቃቀም በማሻሻል መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ አሰጣጥን ማጎልበት ነው፡፡

### 4.5.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. የጤና መረጃ፣ ጥናትና ምርምር እና የእውቀት አስተዳደርን ለማጎልበት በዘርፉ በሁሉም ደረጃ በሰው ኃይል፣ በተቋማት ግንባታና በመዋዕለ-ንዋይ አቅም መገንባት፤
2. በአገር አቀፍ ደረጃ የጤናና ጤና ነክ የጥናትና ምርምር የትኩረት መስኮችን በመለየትና በመቅረጽ ተገቢውን ግብዓት ማቅረብ፣ ይህንንም የሚከታታልና የሚያግዝ አገራዊ የጤና ምርምር መማክርት ጉባኤ ማጠናከር፤
3. ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮሩ፣ ችግር ፈቺና ተግባራዊ የምርምር ስራዎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ፤
4. በምርምር ተግባር ጥብቅ ሥነ-ምግባር መኖሩንና መከተሉን ማረጋገጥ፤
5. የጤና አገልግሎትን ለማጠናከር የሚረዱ የጥናትና ምርምር ማዕከላት በየክልሉ በማስፋፋት ጥናትና ምርምርን ማጠናከር፤

6. በየደረጃው መረጃን መሰረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ አሰራር የሚያሳልጥ የተቋማት ዓቅም መገንባት፤
7. የጤናና ጤና ነክ መረጃ አያያዝና አጠቃቀም የሚኖረው ሚና ለማዳበር ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና ለዚሁ አላማ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን መጠቀም፤
8. ሕብረተሰቡ በየአካባቢው ያለውን ምልከታና ተሞክሮ በተደራጀ መልኩ በመተንተን የራሱንና የአካባቢውን ጤናና ደህንነት በራሱ የሚያሻሽልበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
9. ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መረጃ ስርዓት በማጠናከር በመረጃ የተደገፈ የውሳኔ አሰጣጥ ማጎልበት፤
10. የጤና ተቋማትና ስርዓቱ ዘወትር የሚማሩና ለለውጥ ዝግጁ ለማድረግ የእውቀት ማዕዳቸውን/ማእከል የሚያጎልበት የእወቀት አስተዳደር ስርዓት ማበጀት፤
11. የህብረተሰቡን ጤና ለማሻሻል የሚያግዙ አዳዲስና አዋጭ ንድፈ-ሀሳቦችን የሚያመነጩ ምሁራን የያዘ የአማካሪነት ሚና የሚጫወት ቡድን እንዲኖር በማድረግ በመረጃ ላይ የተመረኮዘ የጤና አገልግሎት ስርዓት እንዲኖር ማስቻል፤
12. የጤና አገልግሎት፣የጥናትና ምርምር እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ትስስርን በማጠናከር የጤና መረጃ፣ ጥናትና ምርምር እና የእውቀት አስተዳደርን ማጎልበት፤
13. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመስራት አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት ማስፈን፤
14. አገር አቀፍ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የምዝገባና ዳሰሳ ስራዎችን በተጣጣመና በተቀናጀ መልኩ የሚያሳልጥ አሰራር መዘርጋት፤
15. የጤና አገልግሎት መረጃ አያያዝና ለጥናትና ምርምር ማዋልን የሚመለከት የህግ ማዕቀፍ ማበጀት፤
16. የጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን አያያዝና አጠቃቀም ለማጎልበት የሚያስችል ሃገራዊ የመረጃ ቋት መዘርጋት፡፡

## 4.6. የመድሀኒት አቅርቦትና የህክምና ቴክኖሎጂን ማሻሻል

ከጤና አገልግሎት መሰረታዊ ግብዓቶች መካከል የመድኃኒት፣ የህክምና መሳሪያዎችና መገልገያዎች (የጤና አገልግሎት ቴክኖሎጂዎች) ይገኙበታል፡፡ የመድኃኒትና የጤና አገልግሎት ቴክኖሎጂዎች በተለይም የመሰረታዊ መድኃኒት አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም አሁንም ከጤናው ዘርፍ አንኳር ችግሮች መካካል ዋነኛው እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ በአጠቃላይ በጤናው ዘርፍም ሆነ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ደረጃ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይና የገንዘብ ወጪ ከሚጠይቁ የህክምና አገልግሎቶች መካከል የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ይገኙበታል፡፡

የመድኃኒትና የጤና አገልግሎት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ አጠቃቀምም ሆነ አወጋገድ በአግባቡና በስርዓት ካልተመራ ለከፍተኛ የሐብት ብክነት ሊያጋልጡ ከሚችሉ የጤና አገልግሎቶች መካከል ከመሆኑም በተጨማሪ ህብረተሰቡንም ላልተፈለገ ህመምና ስቃይ በማጋለጥ ኑሮው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም

የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ በበቂ ሁኔታ ማቅረብ፣ የሀገር ውስጥ ምርትንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማበረታታት፣ ምርምርና ስርጸት፣ ጥራትና ቁጥጥርን ማረጋገጥ፣ የህክምና ግብዓቶችን በተገቢው ሁኔታ መጠቀምና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የህክምና ግብዓቶች ስርዓትን በጠበቀ መልኩና የአካባቢ ብክለትን በማያስከትሉ ሁኔታ እንዲወገዱ ማድረግ የዚህ ፖሊሲ የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡

### 4.6.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

የዚህ ፖሊሲ አቅጣጫ ዋነኛ አላማ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የመድኃኒትና ሌሎች የጤና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ለሁሉም ዜጎች መድረስ መቻላቸውን ማረጋገጥና ሀገራዊ አቅም በመገንባት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማስቻል ነው፡፡

### 4.6.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ያለመቆራረጥ በሁሉም ጤና ተቋማት እንደየደረጃቸው መኖሩን ማረጋገጥ፣
2. የመድሀኒት፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችና ሌሎች ግብአቶችን በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ሁሉም የጤና አገልገሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ያለማቋረጥ ማቅረብ የሚችል ጠንካራ የአቅርቦት ሠንሠለት አስተዳደርን መገንባት፤
3. አግባብነት ያለው የመድኃኒት አጠቃቀም ስርዓት እንዲሰፍን በማድረግ የመድሀኒቶችን ፈዋሽነት ማረጋገጥ እና መድሃኒት የተለማመዱ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር፤
4. የመድሀኒት እና የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች አጠቃቀም አግባብነት ተጠቃሚውን ባማከለ መልኩ እንዲሆንና ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመቆጣጠር ሚያስችሉ አሰራሮችን መዘርጋት፤
5. ጥቀም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ለህብረተሰብ ጤና ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉ ኬሚካሎች፣መድሀኒቶች፣ መገልገያ መሳሪያዎች እና ሌሎች መወገድ ያለባቸው ቁሳቁሶች የማከማቸትና የማስወገድ ስራዎችን የአካባቢ ብክለትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መከወን፣ ለዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተቀናጀ የማከማቻና ማስወገጃ ስርዓት ማበጀት፤
6. የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ጥገናና እንክብካቤ አገልግሎትን ማስፋፋት፤
7. በመንግስት በሚከናወነው የህክምና መገልገያዎች እና መድሃኒቶች ከክምችት እስከ ስርጭት ባለው ሂደት ውስጥ እና መገልገያ መሳሪያዎች ጥገና ላይ አዋጭ የሆኑ ሂደቶች እየታዩ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት ማድረግ፤
8. የጤና ቴክኖሎጂ ወጥነት፣ አግባብነትና አጠቃቀምን የሚዳስስና ምክረ-ሀሳብ የሚሰጥ እንዲሁም የቴክኖሎጂዎችን ጠቃሚነት ክትትልና ግምገማ የሚያደርግ ስርዓት መዘርጋት፤

9. አዳዲስና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ የጤና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን አጠቃቀም፣ ስርጭትና አተገባበር የሚጠቁም የጤና ተቋማት ስርጭትና አሰፋፈርን መሰረት ያደረገ አገር አቀፍ ፍኖተ-ካርታ የሚያዘጋጅና ተፈጻሚነቱን የሚከታተል ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፤
10. የመድሀኒት፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችና ሌሎች ግብአቶችን በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ማበረታታት በተለየም የግሉ ዘርፍ በዚህ ረገድ እንዲሳተፍ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፤
11. የጤና ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ለማጎለብት የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር፤
12. የመድሀኒት፣ የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች እና ሌሎች የጤና ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀምና ቁጥጥር የተመለከተ የፖሊሲና ስተራቴጂ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤

## 4.7. የጤና ቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር

የጤና አገልግሎት ተገቢውን ጥራትና ደረጃ በጠበቀ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ ከሚያስፈልጉት አንዱና ዋነኛው የአገልግሎትና ግብዓት ጥራት ለማረጋገጥ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ላይ የተጠናከረ የጤና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

የጤና ቁጥጥር ስርዓቱ በዋነኛነት የሚከናወነው ህብረተሰቡን የቁጥጥሩ ባለቤት እንዲሆን በማድረግ የህብረተሰቡን የጤና ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉዳት በሚያስከትሉ ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡ ለጤና አገልግሎቱ በግብዓትነት በሚውሉ መድኃኒቶች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች፣ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ ሳብስታንስና እንዲሁም ሕብረተሰቡ የሚጠቀምባቸው ምግብና ሌሎች በጤናው ላይ ተጽዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ግብዓቶች ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ፣ የጤናና ጤናነክ አገልገሎትን የሚሰጡ የጤናና ጤና ነክ ተቋማት ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን፣ የሚሰጡትም አገልግሎት በተገቢው መስፈርት መሠረት መሆኑንና አገልግሎቱን ለመስጠት በመስኩ የተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች ብቃት ያላቸውና ስነምግባርን የተላበሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

### 4.7.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

- ሕብረተሰቡ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የጤናና ጤናነክ አገልግሎቶችና ግብአቶች ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

### 4.7.2. ስልቶች

ይህንን ዓላማ ለማስፈፀም መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፡፡

1. ህብረተሰቡ ጤናውን ራሱ በራሱ ለመጠበቅ እንዲችል እንዲሁም የቁጥጥሩ ባላቤት እንዲሆን ለማድረግና ዘርፈ ብዙ የቁጥጥር ሥራዎችን መሥራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤
2. ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚቀርቡ ምግቦች ጥራትና ደህንነት፣ የመድሀኒቶች ጥራትና ደህንነት፣ ፈዋሽነትና አግባባዊ አጠቃቀም ቁጥጥር ማድረግ፤
3. የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶች፣ ትምባሆና ሌሎች የማህበረሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ አደንዛዥና ሱስ አስያዥ ንጥረ ነገሮች ላይ የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤
4. መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃትና ደረጃ እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጥ ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ እንዲሆኑ ቁጥጥር ማድረግ፤
5. የጤና ባለሙያዎች ብቃት፣ ሙያዊ ስነ ምግባር ለማረጋገጥ የሚያስችል የጤና ባለሙያ ማህበራትን ያሳተፈ የቁጥጥር ስርዓት እንዲጠናከር ማድረግ፤
6. ህብረተሰቡ የሚኖርበት አካባቢ ለጤና ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቀናጀ የሀይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ቁጥጥር ማድረግ፤
7. በእርዳታ ከአገር ውጭ የሚመጡ መድኃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች ጥራታቸውና ደህንነታቸው እየተረጋገጠ እንዲገቡ ማድረግ፣
8. ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለውና ተደራሽና ውጤታማ የሆነ የተቀናጀ የጤና ቁጥጥር ስርዓት መዘረጋት፤
9. በሰው ሀይልና በቁጥጥር መሠረተ ልማት የተጠናከረ አቅም ያለው የጤና ተቆጣጣሪ አካል እንዲኖር ማድረግ፤
10. የጤና ቁጥጥሩን ለማጠናከር የሚያስፈልጉ የተለያዩ ጥራት ማረጋገጫ ላቦራቶሪዎችን ማደራጀት፤
11. በቴክኖሎጅ የተደገፈ የጤና ቁጥጥር አሰራር መዘርጋትና የቁጥጥር መረጃ ሥርዓቱ ዘመናዊ እንዲሆን ማድረግ፤
12. ህገወጥ የምግብ፣ የመድኃኒትና ሌሎች የጤና ግብዓቶች ዝውውር እንዲሁም ህገወጥ የጤና አገልግሎትን ለመግታት የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት መዘርጋት፤
13. ከጎረቤትና ከሌሎች አገሮች ጋር እንዲሁም ከአሁጉራዊና ከአለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ለጤና ዕድገት አስተዋጽኦ በሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በመተባበር፣የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፤ ለጤና ጠንቅ የሚሆኑ ነገሮችን አብሮ መቆጣጠር፤
14. የጤና ቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከርና በተቀናጀ መልኩ ለማከናወን የሚያስፈልጉ መድሀኒት፣ የምግብ፣ የህክምና ቴክኖሎጂና የመሳሰሉ ፖሊሲዎችን፣ የህግ ማዕቀፎችና ደረጃዎች ማዘጋጀት፤

## 4.8. የጤና ክብካቤ ገንዘብ ምንጭ እና አጠቃቀም ማጎልበት

በቂ የሆነ የመዋዕለ-ንዋይ አቅርቦት የጤና አግልግሎትን በበቂ ሁኔታና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለሁሉም ለማዳረስ ከወሳኝ ግብዓቶች መካከል ዋነኛው ነው፡፡ በሀገራችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሊገኝ የሚችል ሀብትን በማሰባሰብና የተሻለ የመዋዕለ-ንዋይ አቅም በመፍጠር ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት በረካታ የጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን ወደ ስራ የማሰማራት፣ የጤና ተቋማትን የመገንባት፣ የህክምና ገብዓቶችን የሚሟላት ስራዎች ተከናወነዋል፡፡ በዚህም ሳቢያ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ይህንን ተከትሎም አመታዊ የጤና አገልግሎት አጠቃላይና የነፍስ ወከፍ የጤና ወጪ ከጊዜ ወደ ጊዜ  እየጨመረ መጥቷል፡፡ ቢሆንም በየጊዜው እየናረ ያለው የጤና አገልግሎት ወጪ፣ ትኩረት የሚፈልጉና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ የጤና ጉዳዮች መበራከትና የማህበረሰቡ የጤና አገልግሎት ፍላጎት መጨመር ጋር ተያየዞ የሚፈለገውን ያህል ተደራሽነትና የጥራት ደረጃ ያለው የጤና አገልግሎት ለማቅረብ ከፍተኛ ርብርብ ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም እስከአሁን ያለው የጤና አገልግሎት መዋዕለ-ንዋይ ዋነኛ ምንጭ በውጭ እርዳታ በመሆኑና የዚህ ምንጭ ዘለቄታነት የሌለው መሆኑ በቀጣይነት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብም ሆነ እስከአሁን የተገኙትን ውጤቶች ለማስቀጠል የሚያስችል የጤና አገልግሎት ወጪዎችን በሀገር ውስጥ ሀብት ለመሸፈንና ራስን ለመቻል የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ስለሆነም አስተማማኝና ዘላቂ የሆነ የጤና መዋዕለ-ንዋይ የማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል ስርዓት ማበጀት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጤና መድህንን በተጠናከረ መልኩ መተግበር ዋነኛው የጤናው ዘርፍ የገንዘብ ምንጭ ከመሆኑም ባሻገር ዜጎች ለጤና አገልግሎት ወጪ የሚውል ገንዘብ እጦት ሰጋትን በመቀነስ የተረጋጋ ህይወት እንዲመሩ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የገንዘብ አቅምን ለማዳበር የሚያስችሉ አማራጮችን ለመፈለግ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡

### 4.8.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

ለጤና አገልግሎት የሚውል መዋዕለ-ንዋይ በበቂና ራስ-አገዝ ሁኔታ በማሰባሰብ ሁሉ-አቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን፣ ጥራትና ፍትሀዊነት ባለው መልኩ እንዲገኙ ማስቻልና እንዲሁም ዜጎችን በጤና አገልግሎት ወጪ ሳቢያ ከከፋ የኢኮኖሚ ጫና መታደግ ነው፡፡

### 4.8.2. ስልቶች

ይህንን የፖሊሲ አቅጣጫ  ዓላማ ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች ይተገብራል፤

1. ለጤናው ዘርፍ በቂና ዘለቄታዊ ሀብትን ከተለያዩ ምንጮች የማግኛ ዘዴዎችን ማጠናከር፤
2. የጤና አገልግሎት ለህዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ የመንግሰት ሃብት መመደብ፤
3. የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ትብብርን በማጠናከር የዘርፉን የገንዘብ ዓቅም ማጎልበት፤

4. የጤና አገልግሎቱን አቅርቦትና ጥራትን ለማሻሻል የጤና ተቋማቶች ገቢያቸውን የሚጠቀሙበት አሰራር ማጠናከር፤
5. በመልካም ፈቃድ የሚደረጉ የግለሰብና የማህበረሰብ መዋጮዎችን በማበረታታት የህብረተሰቡን ኣሳታፊነት ማጠናከር፤
6. መንግስት የጤና መድህን የህክምና ሽፋንን በማስፋትና በማቀናጀት በተጠናከረ፣ አንድ-ወጥ በሆነ ስርዓትና ብዙሀኑን ባሳተፈ መልኩ መተግበር፤
7. መንግስት የጤና መድህን ስርዓትን ለማስተዳደር የሚወጣውን አስተዳደራዊ ወጪ መሸፈን፤
8. በመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ውስጥ የታቀፉ አስፈላጊ የጤና ፓኬጆች እና የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ህክምና በመንግስት የህክምና ተቋማት ያለክፍያ እየተሰጡ ያሉትን ማስቀጠል፤
9. ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ አገልግሎቶች ዝቅተኛ ገቢ ላለቸው ዜጎች ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ አሰራሮችን መዘርጋት፤
10. ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የፋይናንስ ስርዓት፣ የሰው ኃይል አደረጃጀቶችና አሰራሮች እንዲኖሩ ማስቻል፤
11. የጤና ክብካቤ መዋዕለ-ንዋይን አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና፣ ትንበያን የተመለከተ ስትራቴጂክ ሰነድ ማዘጋጀት፣ እንዲሁም የአፈጻጸም ብቃትን ማሻሻል፤

### 4.9. የጤና ስርዓት አመራርና አስተዳደር ማጠናከር

የጤናው ስርዓት አስተዳደርና አመራር የዘርፉን የፖሊሲ አቅጣጫዎች በተከተለ መልኩ የዘርፉን ምሰሶዎች በማቀናጀት የሚጠበቁትን ውጤቶች ማሳካት ነው።

ኢትዮጵያ ላስመዘገበቻቸው በጎ የጤና ውጤቶች በየደረጃው የተስተዋለው የመሪነት ሚናና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ተጠቃሽ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ ነው። ለብዙሃኑና ለዝቅተኛ ገቢ ላለው ያጋደሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤ እንዲሁም የተለጠጡ ግቦችን ያነገቡ እቅዶችን በመንደፍ፤ በፖሊሲዎቹ፣ ስትራቴጂዎቹ እና ዕቅዶቹ ዙርያ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በተለይም ህዝቡ በማነቃነቅ እና ለተግባራዊነታቸው ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በተቋማት ብዛት፣ በሰው ኃይልና ሌሎች ግብዓቶችን በማሟላት በ1987 ዓ.ም. ከነበረበት 40 በመቶ ወደ 98 በመቶ ማድረስ የአመራሩ ድርሻና የአስተዳደር ስርዓቱ አጋዥነት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ለጤና አገልግሎት መሻሻል የሚስፈልጉ የመዋዕለ-ንዋይ አቅምን ለማጎለበት ሀብት በማሰባሰብና ለታለመለት አላማ በማዋል እንዲሁም የልማት አጋሮችን በአንድ የጋራ እቅድ ስር እንዲሰሩ በማድረግ አበረታች ውጤቶች ተስተውለዋል።

ነገር ግን የጤናውን ዘርፍ ወደፊት ለማራመድ ማነቆ ከሆኑ ጉዳዮች መካካል የመልካም አስተዳደር ጎዳዮች ዋነኞቹ ናቸው። የጤና አገልግሎትን ለህብረተሰቡ ያለእንግልትና

በሚጠበቀው ጥራትና ተደራሽነት ለማቅረብ መጠነ ሰፊ የመልካም አስተዳዳር ማስተካከያ ስራዎች መሰራት አለባቸው፡፡

የጤና ስርዓት አመራር የዘርፉ ራዕይን ሰንቆ በየወቅቱ የሚያጋጥሙትን ክፍተቶችና ተግዳሮቶች እየለየ የሚፈታ፣ ውጤትን ማዕከል ያደረገ፣ በየጊዜው ከሚቀያየሩ ሁኔታዎች ጋር ማለትም የጤና ኩነቶች፣ የማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ እና ፓለቲካዊ ሁኔታዎች ጋር እራሱን እያጣጣመ የዘርፉን ስራዎች የሚመራ እንዲሁም ማህበረሰቡና ፈፃሚውን የሚያስተባብር ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ መልካም አስተዳደር የሰፈነበት እንዲሆን የሕግ የበላይነት፣ የጋራ መግባባት፤ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ አሳታፊነት፣ አካታችነትና ፍትሃዊነት ለሕዝብ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ሰጪነት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነት መርሆችን ይተገበራል፡፡

### 4.9.1. የፖሊሲ አቅጣጫው ዓላማ

የጤናው ዘርፍ ራዕይ የሰነቀ፣ የህብረተሰቡን ጥቅም ያስቀደመ፣ ቀንና ሌት የሚተጋ ውጤታማ የጤና ስርዓት አመራር ኃይል እንዲፈጠር በማድረግ የልማትና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ተግባራዊ ልዕልናን ማስረፅ፡፡

### 4.9.2. ስልቶች

*ይህንን ዓላማ ለማስፈፀም መንግስት የሚከተሉትን ስልቶች የተገብራል፤*

1. የጤናው ዘርፍ የአመራር አካላትን የልማትና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ተግባራዊ ልዕልናን የሚያሰርፅ ቀጣይነት ያለው የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና በመስጠት የህብረተሰቡን ጥቅም የሚያስቀድሙ ልማታዊ አስተሳሰብ ያለቸው መሪዎች መፍጠር፤
2. እያንዳንዱ ወረዳ የጤና አገልግሎትን ራስ-አገዝ በሆነ መንገድ የማቀድና የመተግበር አቅምን ከወረዳ ጤና ፅሕፈት ቤት አደረጃጀት፣ የአሰራር ስርዓትና አስተማማኝ የመዋዕለ-ንዋይ አቅርቦት አንጻር በመቃኘት የወረዳ ትራንስፎርሜሽን እንዲፈጠር ማስቻል፤
3. መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የህዝብ ድምጽ የሚሰማባቸውና የህብረተሰቡን ባለቤትነት የሚያጠናክሩ የህዝብ አደረጃጀቶችና የብዙሃን መገናኛ አውታሮችን በመጠቀም በዘርፉ የመልካም እተዳደር እንቅስቃሴዎች ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ፤
4. የጤና አገልግሎትን ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነትና ጥራት ለማረጋገጥ በሁሉም ደረጃዎች የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓትን ማጠናከር፤
5. በጤናው ዘርፍ የአስተዳደርና አመራር ላይ ሴቶችን እኩል ተሳታፊ ለማድረግ በተለይም በጤና ዘርፍ የሚኖሩ የሴት አመራሮች ቁጥር ከወንዶች እኩል ማድረግ፤
6. ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን በማብቃት የህዝቦችን የጤና አገልግሎት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ፤

7. የዘርፈ ብዙ ትብብርን ማጎልበት፣ ለተግባራዊነቱም አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
8. አስፈላጊ በሆነበት ሁኔታ በጤና ተቋማት የህክምናና ህክምና ያልሆኑ (የድጋፍ) አገልግሎቶች፣ እንዲሁም የአስተዳደር አገልግሎቶች በሌሎች አቅሙ ባላቸው ተቋማት እንዲከናወን ማድረግ፤

## 4.10. የባህል ህክምና ማሻሻል

ህብረተሰቡ የፈውስ ህክምና ለማግኘት ከሚያዘወትራቸው ህክምና አማራጮች መካከል የባህል ህክምና አንዱ ነው። ይህ ህክምና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የኖረ ልማዳዊ ድርጊት ሲሆን ከዕፀዋት፣ እንስሳትና ማእድናት የሚገኙ ንጥረ ነገሮችን በባህላዊ መንገድ በመቀመም የሚሰጥ ህክምናን፣የአጥንት ስብራትና ውልቃት ባህላዊ ህክምናን፣ ባህላዊ የወሊድ አገልግሎትን እንዲሁም መንፈሳዊ የባህል ህክምናን ያካትታል። የባህል ህክምና ህብረተሰቡ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከሰው ልጅና እንስሳት ጋር ያላቸውን መስተጋብር ለዘመናት በማስተዋል ያከማቸው እውቀት፣ ብልሃት፣ ክህሎትና ድርጊቶች ውጤት እንደሆን ይታመናል። በዘመናዊ ህክምና ውስጥ የምናያቸው ሳይንሳዊ ግኝቶች በአብዛኛው ተፈጥሮን የማስተዋልና ሚስጥሯን በሳይንሳዊ መንገድ የመፈተሸና ወደ ቴክኖሎጂ ምርቶች የመቀየር ሂደት ውጤቶች ናቸው። በመሆኑም ይህንን የህብረተሰብ እውቀትና ክህሎት በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ጥናትና ምርምሮችን ማድረግ ከፍተኛ ተኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህም የባህል መድሀኒቶችን ጠቃሚ ጎን ለማጎልበትና ከዘመናዊ የህክምና ዘዴዎች ጋር ለማቀናጀት የሚረዱ ዘዴዎችን ለመቅረጽ ያስችላል። በተጨማሪም በርካታ ዜጎች የባህላዊ መድሃኒቶች ተጠቃሚና የባህል መድሃኒት አዋቂ ተከታታይ በመሆናቸው፣ ይህን ሁኔታ ህብረተሰቡ እውቀቱና ልምዱ በሌላቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች ለአደጋና ለምዝበራ እንዳይጋለጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

የባህል ህክምና በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱ ውስጥ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲኖረው የሚያስችሉ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል።

### 4.10.1. የፖሊሲ አቅጣጫው አላማ

የባህል ህክምና ጥናትና ምርምር፣ የጤና አገልገሎት አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር ለህብረተሰቡ ጤና አዎንታዎ አስተዋጽኦ እንዲየደርግ ማስቻል

### 4.10.2. ስልቶች

1. የባዮቴክኖሎጂ ስራዎችን በባህል ህክምና ዙሪያ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ ጥናትና ምርምር ማካሄድና አጠቃቀሙን ማሻሻል፤

2. የባህል ህክምናን ከዘመናዊ ህክምና ጋር አቀናጅቶ የጤና አገልግሎት መስጠት የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት፤
3. የባህል ህክምና በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱ ውስጥ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲኖረው የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች፣ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን ማጠናከር፤
4. ህብረተሰቡ እውቀቱንና ልምዱ በሌላቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች ለአደጋና ለምዝበራ እንዳይጋለጥ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
5. የጤና ቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከር የሚያስፈልጉ የባህላዊ ህክምና ስተራቴጂዎች ማዘጋጀትና መተግበር፤

## 4.11. ጤና በሁሉም ፖሊሲዎች

ጤና በሁሉም ፖሊሲዎች ማለት የዜጎችን ጤናና ደህንንት በዘላቂነት ለማረጋጋጥ ሁሉም ዘርፎች (ሴክተሮች) በፖሊሲዎቻቸው፣ ስተራቴጂዎቻቸው፣ የድረጊት መርሃ-ግባራቸውና የተግባር እንቅስቃሴዎቻቸው የዜጎችን ጤና ታሳቢ ያደረጉ ውሳኔዎችን ማሳለፍና ለተግባራዊነቱም የዘረፈ-ብዙ ተደጋጋፊ ርብርብ የሚጠይቅ የልማት መንገድ ነው። የጤና ፖሊሲዎችና መርሀ-ግብሮች (ስራዎች) ሌሎች ዘርፎች ውጤታማ እንዲሆኑ ወሳኝ የሆነውን የሰው ኃይል ጤናና ደህንነት ማሻሻልን ያለመ ሲሆን ሌሎች ዘርፎች ደግሞ ፖሊሲዎቻቸውንና መርሀ-ግብሮቻውን ለህብረተሰቡ ጤና ጠንቅ እንዳይሆኑ ከመከላከል ባሻገር የዜጎችን ጤና የሚያበለጽጉ እንዲሆኑ በማድረግ በሁሉም ዘርፎች የጋራ ርብርብ ጤናማ፣ ምርታማና የበለጸገ ህብረተሰብ የመፍጠር ራዕይን ለማሳካት ይህ የልማት መንገድ ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል።

የጤና ጉዳዮች በሌሎች ሴክተሮች ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጣቸው የሚያስችሉ አሰራሮችን ለማበጀትና ለተግባራዊነታቸው ተገቢውን ድገፍ ለማድረግ በየተወሰኑ ጊዜያት የፖሊሲና ስትራቴጂ ዳሰሳዎችና ትንተናዎችን ማድረግ፣ የትብብር ማእቀፎችና ፎረሞች ማዘጋጀት፣ የጋራ መዋዕለ-ንዋይ መመደብ፤ የጋራ ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ ያስፈልጋል።

ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ከሌሎች ሴክተሮች ጋር በጋራ የሚሰሩ የጤና ስራዎችን በመለየት፣ የጋራ እቅድ በመንደፍ፣ የአተገባበር ስልቶችና መከታተያ ማእቀፎች በማዘጋጀት መተግበርና ቀጣይ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለመከለስ የሚያግዙ መረጃዎችን በጋራ በመቀመር የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቱን ፍትሃዊና ዘላቂ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

### 4.11.1. የፖሊሲ አቅጣጫ አላማ

የሁሉም ዘርፎች ፖሊሲዎች ጤናን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን በማረጋገጥ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ጤናማ፣ አምራችና የበለጸገ ማህበረሰብ መፍጠር

### 4.11.2. ስልቶች

1. አግባብነት ያለው የምግብና የሥርዓተ-ምግብ ስተራቴጂ መቅረጽና መተግበር፤
2. የህዝብ ዕድገትን በእቅድ ለመምራት በተሟላ የህብረተሰብ ጤንነትና የቤተሰብ እቅድ ማጠናከር፤
3. ለገጠርና ለከተማ ሕዝቦች ንጹህና በቂ የመጠጥ ውሃ በዘላቂነት የሚዳርስበትን መንገድ ማፋጠን፤
4. ከሌሎች በዘርፉ ከሚንቀሳቀሱ ሴክተር መስሪያ ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሁም አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር የተsማትን የዉሀ፤ የሳኒቴሽን እና ሐይጅን መሰረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን ማሻሻል፤
5. የሰው፣ የቤት፣ የእርሻና ኢንዱስትሪ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት ተስማሚ መንገዶችን ማዘጋጀት፣ እንደአግባቡም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ዘዴ ማበረታት፤
6. የመኖሪያ ቤቶችን፣ የስራ ስፍራዎችንና የመዝናኛ ቦታዎች አሠራርና አያያዝ ጥራት የሚያሻሽሉ እርምጃዎችን ማጎልበት፤
7. የአየር ንብረት ለዉጥ እና ብክለት የሚያስከትለዉን ችግር ለመቀነስ ብሎም ለመከላከል ከሌሎች ባለድረሻ አካላት ጋር በመተባበር ዉጤታማ የሆኑ ስልቶችን በመንደፍ እና በመተግበር ጤናማ የመኖሪያ እና የስራ አካባቢ እንዲፈጠር አስተዋፆ ማድረግ፤
8. በፋብሪካዎችና ተቋማት ውስጥ በሚቋቋሙ መዋለ-ህጻናት፣ትምህርት ቤት፣ የጤና አገልግሎትና የሥርዓተ-ምግብ መርሀ-ግብሮች ዝግጅት፣ግንባታና አተገባበር ላይ መሳተፍ
9. የአካልና የአእምሮ ጤና ጉዳተኞች፣ ደጋፊ ለሌላቸው ህጻናትና አረጋውያን እንክብካቤ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚቋቋሙ አገልግሎቶች ማስፋፋት ተግባር መሳተፍ፤
10. ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ አህጉራዊና አለማቀፋዊ የጤናና ጤና ነክ ጉዳዮች ላይ በትብብር መስራት፤
11. ጤናና ጤና ነክ ህጎችንና ደንቦችን ወቅታዊ ማድረግ፣ አዳዲስ የጤናና ጤና-ነክ ጉዳዮችን ለማስተናገድ ተጨማሪ ህጎችንና ደንቦችን ማውጣት እንዲሁም ወደ ተግባር መተርጎማቸውንና ተፈጻሚነታቸውን የሚያረጋግጡ አሰራርና አደረጃጀቶችን ማጠናከር፤

12. ዘርፈ-ብዙ ትብብር የሚሹ መርሃ-ግብሮችን በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መስራት፡

- የሥርዓተ-ምግብ ዘርፈ-ብዙ መርሃ-ግብር፣
- የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር፣
- የሀይጂንና አካባቢ ጤና፣
- የሥነ-ህዝብ እና የማህበራዊ ዋስትና ጉዳዮች፣
- የስራ ቦታ ጤናና ደህንነት፣
- የሥርዓተ-ጾታ፣
- የመንገድ ትራፊክና ሌሎች አደጋዎች መከላከልና ቁጥጥር፣
- የትምህርት ተቋማት ጤና፣
- የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት እና የማረሚያ ቤቶች ጤና፣
- ከእንስሳትወደ ሰው የመተላለፉ በሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር፣
- የመሠረተ-ልማት ግንባታ፣
- ከፍተኛ አገራዊ የልማት ፕሮጀክቶች የተያያዙ የጤናና ጤና ነክ ጉዳዮች (የኢንዱስትሪ ጋር የተያያዘ ብክለት እና የስራ ሁኔታ፣ ሰፋፊ የኃይል ማመንጫና የመስኖ ፕሮጀክቶች ከቤቶች ልማት እና የመንደር ማሳባሰብ ወዘተ)፣

# ክፍል አምስት
# የፖሊሲው አተገባበር

## 5.1. ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር

በየደረጃው ያሉትን ተቋማት አቅም ማጎልበት ፖሊሲውን ወደ ተግባር ለመተርጎም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ተቋማዊ የአቅም ግንባታ በጤናው ዘርፍ በየደረጃው ያሉትን ተቋማት አግባብነት ባለው የሰው ኃይል፣ ፋይናንስ እና ሌሎች ግባኣቶች በማጠናከር ለተጠቃሚው ምላሽ ሰጪ የአሰራር ስርዓትን በየጊዜው በማሻሻል ተልዕኮቸውን መወጣት ማስቻል ይኖርበታል። ተቋማዊ አቅምን የማጠናከር ስራዎች አገሪቱ ትኩረት በመስጠት የምትሰራቸውን የጤና ፕረግራሞች፣ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ የሚሹ ስራዎች፣ የማህበረሰብ አቅም ግንባታዎች ዙሪያ ላይ ያጠነጠኑ ይሆናሉ።

ትኩረት ከሚሰጣቸው የጤና መርሃ-ግብሮች እና የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት አሃዶቹንና የሆስፒታል የአገልግሎት ጥራትን በማሻሻል የሚተገበሩ ይሆናሉ።ስለሆነም የጤና አገልግሎት አወቃቀር ለህዝቡ የጤና ፍላጎት ምላሽ ሰጪ ሆኖ እንዲደራጅ ይደረጋል። ተገቢውን ጥናት በማካሄድም በገጠር፤ በአርብቶ አደር እና በከተማ ደረጃ አደረጃጀቱ እንዲታይ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ አጠቃላይ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችን የሚመሩና የሚያስተባብሩ በፌደራል፣ ክልል፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ የሚገኙት ተቋማትም ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚጠናከሩ ሲሆን በተለይም ደግሞ ለወረዳ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

እንዲሁም ለጤና አገልግሎቱ መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖራቸው የምርምርና ጥናት፤ የስልጠና፤ የደምና ሌሎች የሰውነት አካላት ባንክ፤ እና ሌሎች የተለያዩ ተቋማት እንደየአስፈላጊነቱና የአገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን በየደረጃው እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ይደረጋል።

ትኩረት ከሚሰጣቸው የዘርፈ ብዙ ጤናና ጤና ነክ የጤና መርሃ-ግብሮችን ወደ ተግባር ለመተረጎም የሚያስችሉ የአቀም ግንባታ ስራዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በጋራ ይሰራሉ።

ከላይ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌሎች አግባብ ያላቸው ስራዎች ውጤታማ ለማድረግ ህብረተሰቡ በኃላፊነትና በባለቤትነት መንቀሳቀስ ወሳኝ በመሆኑ መረጃ በመስጠት፣ የህግ ከለላ በማበጀትና ክህሎቱ እንዲዳበር በማድረግ የህብረተሰቡን አቅም ማጎልበት ተገቢ ይሆናል። ለዚህም የተጀመሩትን የጤና ልማት ሰራዊት አደረጃጀት አጠናክሮና አዘምኖ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መስራት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

## 5.2. የሕግ ማእቀፎችን ማበጀትና የማስፈጸሚያ ስልቶችን ማጎልበት

ይህን ፖሊሲ ወደ ተግባር ለመተርጎም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንደአስፈላጊነቱ የሕግ ማዕቀፍ ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ የድንጋጌዎቹን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

## 5.3. ስትራቴጂክ እቅዶችን፣ ፖሊሲዎች፣ ፍኖተ ካርታዎችንና የአተገባበር መመሪያዎችን እንደየአስፈላጊነቱ በመንደፍ ወደ ተግባር መመንዘር

ትኩረት የሚሰጣቸው የጤናና ጤና ነክ ጉዳዮች ዙሪያ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ ፍኖተ ካርታዎችንና የአተገባበር መመሪያዎችን እንደየአስፈላጊነቱ በመንደፍ ወደ ተግባር መመንዘር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ሰነዶች እርስ በርስ የሚናበቡና የተሻለ ቅንጅት በማምጣት የሚፈለገውን ውጤት በዘላቂነት የሚያስቀጥሉ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስት መሰረት የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሀገሪቱን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፤ ይፈፅማል፡፡ የጤናና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ፖሊሲዎች መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁት አገራዊ ፍኖተ-ካርታዎች፣ ስትራቴጂክ እቅዶች እና የአተገባበር መመሪያዎች የህዝቦችን የጤና ፍላጎት ምላሽ ሰጪ ሆነው እንዲዘጋጁ እና የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት እንዲቻል አሰራሩ በሚፈቅደው መሰረት ከክልሎች ጋር በጋራ በመስራት እስከ ወረዳና ቀበሌ በማውረድ እና ከታች ከወረዳና ቀበሌ ጀምሮ ወደ ላይ በማናበብና በማቀናጀት የሚዘጋጁና የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡

በየደረጃው የሚዘጋጁት ፍኖተ-ካርታዎችና ስትራቴጂክ እቅዶች የመንግስት ባለቤትነትና መሪነት አሰራር በተከተለ መንገድ ሁሉም የጤናዉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በቂ ታስትፎና ምክክር እያደረጉበት እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

## 5.4. የክትትልና ግምገማ

የፖሊስውን ውጤታማነት የሚለኩ አንኳር መለኪያዎች በመለየት በየተወሰነ የጊዜ ርቀት መከታተልና መገምገም ተገቢ በመሆኑ ቀጣይ ስተራቴጂዎች ይህንን ታሳቢ ያደረገ የክትትልና ግምገማ ማእቀፍ እንኖራቸው ይደረጋል፡፡

## 5.5. የመዋዕለ-ንዋይ (የፋይናንስ) አቅርቦትና አጠቃቀም

የጤናው ዘርፍ የፋይናንስ አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ የጤና መድህን ዋነኛ መሳሪያ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በርካታ ዜጎችን እንዲያቅፍ ይደረጋል፡፡ ጤናን የማበልጸግና በሽታ የመከላከል ስራዎች አብዛኛውን ዜጋ ለከፍተኛ ወጪ ከሚዳርጉ የጤና እክሎች የሚጠብቁ በመሆናቸው እነዚህን አገልግሎቶች ህብረተሰቡ በባለቤትነት እንዲተግባራቸው የሚያስችሉ የመሰረታዊ ጤና አገልገሎት አሰጣጥን ስርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

የተመረጡና አስፈላጊ የጤና አገልግሎት ፓኬጆችን በመለየት በነጻ የሚሰጡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በተጨማሪም የድሀ-ድሀ የሆኑ ዜጎች በነጻ የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት መንገድ ይመቻቻል፡፡

## 5.6. አስተዳደር

ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር የሁሉንም ባለድርሻ አካላት አቀናጅቶ መስራት ይጠይቃል፡፡ ለዚህም መልካም አስተዳደርን የሚያጎለብቱና እንዲሰፍን የሚረዱ አደረጃጀቶችና አሰራሮች እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የክልል ጤና ቢሮዎች የጋራ የምክክር መድረክ በማጠናከር የሀገሪቱን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ይፈፅማሉ፡፡

እንዲሁም በፌደራል፣ ክልል፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ ከጤና ልማት አጋሮች ጋር የምክክር መድረክ በማጠናከር የአገሪቱን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ እንዲሁም በየደረጃው የሚዘጋጁት ዕቅዶችና መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የአገሪቱን የጤና ሁኔታ ለመጠበቅና ከሌሎች አገሮችም ትብብር ለማጠናከር ከጎረቤት አገሮች፣ አህጉራዊና የዓለምአቀፍ የጤና አጋርነት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ አደረጃጀቶች እና ኮሚቴዎች እንደየአስፈላጊነቱ በማዋቀር የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ይደረጋል፡፡